የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፭
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6th Year No. 35
ADDIS ABABA - 6th June, 2000

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፳፻፭/፲፱፻፺፪ ዓ·ም
የኢትዮ—ሩሲያ የኢኮኖሚ ፡ የሳይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........................ ገጽ ፩ሺ፫፻፲፭

## CONTENTS

Proclamation No. 205/2000
Ethio-Russia Economic, Scientific and Technical Cooperation Agreement Ratification Proclamation ........................................ Page 1315

## አዋጅ ቁጥር ፳፻፭/፲፱፻፺፪

### የኢትዮ—ሩሲያ የኢኮኖሚ ፡ የሣይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነትን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና በሩሲያ ፌዴሬሽን መንግሥት መካከል የኢኮኖሚ ፡ የሣይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ኅዳር ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ·ም· በሩሲያ ሞስኮ ከተማ ላይ የተፈረመ ስለሆነ ፤

ስምምነቱ የሚፀናውና በሥራ ላይ የሚውለው አንደኛው ወገን በሕገ መንግሥቱ መሠረት አስፈላጊውን ሥርዓት አሟልቶ በዲፕሎማሲያዊ መስመር ለሌላኛው ከሚያሳውቅበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተመለከተ በመሆኑ ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮ—ሩሲያ የኢኮኖሚ ፡ የሳይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፳፻፭/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

## PROCLAMATION NO. 205/2000

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE ETHIO–RUSSIA ECONOMIC, SCIENTIFIC AND TECHNICAL COOPERATION AGREEMENT

WHEREAS, an Agreement on Economic, Scientific and Technical Cooperation between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Russian Federation Government was signed at Moscow, Russia, on the 26th day of November, 1999;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall enter into force on the latter date on which either party notifies the other through diplomatic channel upon the fulfillment of its necessary Constitutional requirements;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 6th day of June, 2000;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Ethio-Russia Economic, Scientific and Technical Cooperation Agreement Ratification Proclamation No. 205/2000."

፪· <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በሩሲያ ፌዴሬሽን መንግሥታት መካከል ህዳር ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ሞስኮ ላይ የተፈረመው የኢኮኖሚ ፡ የሳይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል ፡፡

፫· <u>የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር ሥልጣን</u>

የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር ስምምነቱን በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል ፡፡

፬· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል ፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Ratification of the Agreement*

The Agreement on Economic, Scientific and Technical Cooperation between the Government of Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Russian Federation Government signed at Moscow on the 6th day of December, 1999, is ratified.

3. *The Power of the Minister of Economic Development and Cooperation*

The Minister of Economic Development and Cooperation is empowered to implement the Agreement.

4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force as of the 6th day of June, 2000.

Done at Addis Ababa, this 6th day of June, 2000.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE